# <u>ሆንሽዎይ ጋለሞታ</u>

በሕግ በሥርዓቱ- በባህል በወግሽ፣

አባወራ ኖሮሽ- ተከብረሽ እንዳልኖርሽ፣

ዘር ትውልድ አብዝተሽ፣

ወግ ማዕረጉ ደርሶሽ

ያባዳኘው እናት፣

የባ ታጠቅ እናት፣

የነ በላይ እናት፣

የነአሉላ እናት፣

የዘርዓይ ደረስ፣

ስንት አለ 'ሚጠቀስ፣

በታሪክ ሊወደስ።

እናት አገር ጦቢያ፣

የሁላችን መኩሪያ፣

ውብ መቅነትሽ እንደምን ተፈታ፣

ውርጋጡ ሊደፍርሽ- ሆነሽ ጋለሞታ።

በሚስትና በርስት የለም ሲሉ ዋዛ፣

ሕጋዊ ባል ቀርቶ ስርቆት ምነው በዛ?!

የመንደር ወጠጤ ያለአቻ ጋብቻ፣

ማን አውቆ አስተዳደር- ቆይ ብቻ- ቆይ ብቻ።

ምርጫው ተምታታብሽ - ትዳሩን ለማጥበቅ፣

ማጀትሽ ነጠፈ- ጎጆሽን ለማሞቅ፣

ለአንቺ የሚመጥን- አጣሽዎይ እጮኛ፣

ተከብሮ የሚያስከብር- ያልሆነ ዘረኛ፣

ፍትህ የሚያሰፍን- ሕዝብ እንዳይጎዳ፣

በጥቅም ተደልሎ የማይሆን ሰው ባንዳ።

ኧረ እንዴት ተብሎ- ምን ጊዜ ቢጥልሽ፣

ጋጠወጥ ባለጌ እንደምን ሊደፍርሽ፣

ሲያሻው ሊያከራይሽ፣

ሲያሻው ሊወሽምሽ፣

ይመኛል ምን ግዱ- ሊሆን አባወራ፣

ምን ወግ ባህል አለው- ጥንብ አንሳ ጆቢራ።

ምን ይሰማ ጆሮ ፣

ምን ይውጥ ጉሮሮ፣

ባልማእረጓ እናት ሆናለች አውታታ፣

ክብሯን የሚያስመልስ የሚታደግ አጥታ።

አፋፍ ላይ ሁኜ ማን ብየ ልጣራ፣

ያባታጠቅ ያለህ - እሳተ ገሞራ፡

ልጩህ ድምጼ እስኪሰል- ብየ ያየህ ይራዳ፣

ይነሳ እንደሆነ- ሲሰማ ይህን ጉድ።

መቃብር ፈንቅሎ- አንዴ ቢነሳ እርሱ፣

ለባንዳ ሡራዊት- ይሆን ነበር ምሱ።

የሥልጣኔ ጮራ- አየን ባባዳኘው፣

ላገር ብልጽግና ነበር የሚመኘው፣

ዳርድንበር ሊያስከብር የማይወላውለው፣

ጣሊያንን በዐድዋ- በድል አድባየው።

እንኳንስ ጦቢያዎች- ሕዝብ ሙሉ አፍሪካ፣

በተሠራው ሥራ ቆይቷል ሲመካ።

ያሸበረቀውን- የጥቁር ሕዝብ ፍኖት፣

ምንደኞች አቃለው- አሉት ተረት ተረት።

ነብሩ ዓይኑን ታሞ- ፍየሉ ጎበኘው፣

እንዲሉ ሲተረት በኛ ደርሶ አየነው።

የጂማ አባጅፋር ቢሰሙኝ  ልናገር፣

ጎበና አባዳጨው ቃል ይስጡ ምስክር፣

ያአብዲሳ አጋም ታሪኩ ይነገር፣

ቅርንጫፍ ነው ዛፉ የሚገነጠለው፣

ከቶ የትኛው ነው- ጥላና ማረፊያ ሊሆን የሚስማማው፣

ወደ አፋርም ልሂድ የሡልጣኖች አገር፣

የሰው ልጅ መገኛ- የነሉሲ ምድር፣

በኢትዮጵያዊነት ላይ- የለበት ድርድር።

ወደ ምሥራቅ ልጓዝ- በሐረር አባድር፣

ግልጽነት ጨዋታ-ያጠግባል ለራበው- ጦም ውሎ ቢታደር።

ጀጎልን  ልዞረው ድንገት ባገኛቸው አሚር አብዱላሂ፣

ትልቅ ትንሽ ጎሳ- ሓበሻ አንድ ነው- ይሉኛል ወላሂ።

በድዋ ባህል ዕምነት- በገዳ ሥርዓት፣

በህዘን-በደስታ-በጅጌ-በደቦ- በዕድር-ትብብር አብሮነት፣

ውብ አገር ሽሙንሙን- ወግ ማዕረግ ያላት፣

በዘመነ ጥላሸት- ምን መርገም መጣባት?!

የአክሱም ለኛ ባትል- ግሸን ማርያም ምነው፣

ኢትዮጵያን  አትርሺ- ልጅሽን ተማለጂው።

ኧረ ግራ ገባኝ ልጠይቅ ቃልቻ፣

ፈዳ ልበልና ላውጣ በረንተቻ፣

የዘውዱ ጠባቂ- ቆሪጥ እንደሆነ፣

አልጋው ላይ ለወጡት ለአራጆች ወገነ።

በወሎ ዱበርቲ ደጋጎቹ መጀን፣

አንድዬ ገላግለን -የዘር ሰደድ እሳት-አቃጥሎ ሳይፈጀን።

ላንቺም እናት አገር ልናገር ቱማታ፣

ደፍሮ ያስደፈረሽ- የዘመን አለሌ- ይነሳ ከላይሽ አትሁኝ ጋለሞታ።

ማሕፀንሽ ይለምልም - ባንዳ ግን አያፍራ፣

ዘር ይውጣልሽ አቦ - ትውልድ የሚያኮራ፣

ኧረ ልጅ ይውጣልሽ- ታሪክ የሚሠራ፣

ብን ጥን ይበሉ- ያንድነት ደንቃራ።

ኮስትር ዘዳውድ- ከባህር ማዶ

# ቃል ካልተከበረ

ማሰሪያ ማጥበቂያው-ቃል ነበር ቃል ገብቶ፣

ያምናውን ዘንድሮ-የትናንቱን ዛሬ-ላይሆን አባይ ከድቶ።

ቃል መግባት ነበረ- ዛሬም ቢሆን አለ፣

ቁምነገሩ ባይቀር- ዋጋው ባልቀለለ።

ተባዕት ከእንስት- በትዳር ሊጓደን፣

መርሁ ቃል ነበር- ተብሎ ቃልኪዳን።

ጓደኛ ላልከዳ፣

ጎረቤት ላልከዳ፣

ወዳጄን ላልከዳ፣

አገሬን ላልከዳ፣

እያለ ቃልገብቶ- ተናግሮ ቃልሰጥቶ፣

በመሀላ አጽንቶ፣

ቢገኝ ይኸ ከድቶ

ሊጠራ አያመችም ከሰው ተራ ገብቶ፣

ሥዕሉ ሰው ቢመስልም- ሰው አይባል ከቶ።

ቃል ካልተከበር- ዕምነት ካልጠበቀ፣

ሰው መሆን ትርጉሙ- አለቀ ወደቀ።

ለአንድ ዓላማ ስምረት- በጋራ ሊሠሩ፣

በመርሆ ውጥን- ጉዞ ሲጀምሩ፣

እሾህ አሜከላ- ቢሆን መንገድ አጥሩ፣

እደመነሻቸው መጨረሻ ድረስ፣

ሳይነጣጠሉ በኅብረት ለመድረስ፣

የሚችሉ ካሉ ምንኛ ይላልደስ።

ግና ምን ይሆናል- ዳሩ ምን ያደርጋል፣

ዕምነት ውሉን ሳተ ባይጠፋም ያሰጋል፣

የቃልኪዳን ትርጉም- ይዘቱ ይናጋል።

ኮስትር ዘዳውድ- ከባህር ማዶ

# ለእኔ ሲል ማን ይሙት?

መራብ መጠማቴ፣
እርቃን እርዛቴ፣
ጎስቋላ አከላቴ፣
ደሳሳዋ ቤቴ፣
ባዶ ነው ማጀቴ፣
የኑሮ ስንክሳር ፣
ለእኔ ነው ብዙ አሳር።
ጧት ማታ የምሮጥ ፣
ከችጋር ለማምለጥ።
ብማስን-ብኳትን-ቋት የማይሞላልኝ ፣
ገበሬ-ወዛደር----ሁልጊዜ አውታታ ነኝ።
እኔ ጦም እያደርኩ ከፋይ ነኝ ግብር፣
ቤሳ ቤስቲን እንኳ ሳይኖረኝ ቢቀር፣
እንደከብት መነዳት አለብኝ እስር።
ደሳሳ ጎጆዬ ዋጋ ብታወጣ፣
ዕዳ እከፍል ነበር በሓራጅ ተሸጣ።
ከወህኒ የሚሻል አማራጭ ስደት ነው፣
ከትውልድ መንደሩ ምውጣት ለወሰነው።
ከተማም ቢገባ አይመች ወገኔ፣
ቶርቸር ይሉት አል ተብሎ ቦዘኔ።
እንኳን የእኔ ብጤ ትምህርቴ ጅምር፣
ሲሉ ሰምቻለሁ ቦዘኔ መምህር፣
መቼም ደፋር ናቸው ጠቅላይ ሚኒስትር፣
ፀያፍ ቃል ልምዳቸው ሆነው ርዕሰ ብሔር።
ለአራሹ ገበሬ ለነጋዴው ቢሆን፣
መድሎ የሌለበት መች ፍትህ አየን።
ተማሪው መምህሩ-ሲቪሉ ወታደር፣
እልፍ አዕላፍ ሠርቶ አደር፣
ነፃነቱን ያጣ ሁሉም የቁም እስር።
መሆናችን ቀርቶ ሰብአዊ ፍጡር፣
ሆነና ተቸገርን ቀዳሚው ዘርማንዝር።
ከጥቂቶች በቀር ለማን ነው የደላ፣
ተቸርችራ ስታልቅ አገር በደላላ?.
በዘር በኃይማኖት- እርስ በርስ መናከስ፣
መሀላችን ገብቶ- ሥርሰዶ እንዲባባስ፣
የቆመ ሥርዓት ተተክሎ አገራችን፣
ይህንን ለማምከን- ከመላ ምድራችን፣
የማነው ጉዳዩ በዜግነታችን?!

መብቴን ተገፈፍኩ- ጥቃት በረታብኝ፣
አገሬ ክብር አጣች- እኔን ተዋረድኩኝ፣
ፍትህ-እኩልነት- የምል ሰው ከሆንኩኝ፣
ይህ ዕውን እንዲሆን ማን ይሁን መስዋዕት፣
እኔ እዳር- ከቆምኩኝ- ለእኔ ሲል ማን ይሙት?!

ኮስትር ዘዳውድ- ከባህር ማዶ